# መድኃኒታችን በመጽሐፍ ቅዱስ ሲፈታ

በኃይሉ ቸርነት

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 1997 ዓ.ም.

# መድረኮቻችን
# በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

ይህንን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት
ወይም እንደገና ማስተም በሕግ የተከለከለ ነው።

© Hailu Cherenet 2004

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RP 17

**ይህችን መጽሐፍ ዘወትር በአገልግሎቴ ዋጋ ከፍለው አብረውኝ ለቆሙት ባለቤቴና ልጆቼ መታወሻነት አበረክታለሁኝ፡፡**

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ምእመን ፊት ለሚቆሙና ለሚያቆሙ ነው፡፡ ለኢጥቢያ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች፥ ለመድረክ (ፑልፒት ኮሚቴ አባላት፥ ለሰባኪዎችና ለመዘምራን ነው፡፡ መምህር ኃይሉ ቸርነት «ምሰባክ» የሚል አዲስ ቃልም እያስተማረን ነው፡፡ መድረክ የሚለው ቃል ቲያትረኞች ያልሆኑትን ነኝ የሚሉበት፥ ፓስቲከኞች እራሳቸውን ከሚያስተዋውቁበት ቦታ የተለየ መሆኑን ሊያስተምረን ይህንን ቃል የተጠቀመ ይመስለኛል፡፡

እንድ ሥራ ላይ ስንመደብ ሥራውን በሚገባ ለመሥራት እንድንችል ስለዚያ ሥራ የሚለጥ ኮርስ ካለ ያን ኮርስ መውሰድ ጥሩ ነገር ነው፡፡ ለምንመደብበት ኮሚቴ ሁሉ ኮርስ ቢኖር ጥሩ ነው፡፡ ዛሬ አብዛኛው ነገር የሚሰማውና የሚጠፋውም መድረክ ላይ በአዲስ ቃል በምሰባኩ ላይ በሚቆሙት ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ላይ የቀረበው እውነት ምሰባኩ ላይ የሚያቆሙና የሚቆሙት መወሰድ ያለባቸው ኮርስ ነው ብየ አምናለሁኝ፡፡ በባለሙያ የተጻፈ ነው። ወንድም ኃይሉ ቸርነት የመድረክ አገልጋይና መምህርም ነው፡፡

ሽማግሌዎች ሆይ የእግዚአብሔርን መንጋ እንድትጠብቁ፥ እንድትመገቡ (በመድረኩ ላይ በምታቆሙት ሰው እማከኝነት) እንድትመሩት የወንድማችንን ምክር ገንዘብ አድርጉ፡፡ በየግላችሁ እንድ እንድ ምዕራፍ አንብባችሁ በየሰበሰባችሁ በሕብረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ የየራሳችሁን ጥያቄዎችም አክላችሁ እንድትወያዩ ያስፈልጋል፡፡

ያሰብን ተግዳሮት ከፍተኛ ነው፡፡ አካሔዳችን ግን ተመጣጣኝ አይደለም፡፡ በተለይ የእሁድ ጠዋት የአምልኮ ጊዜ ምእመኑ የሚማርበት ዋና ጊዜ ነው፡፡ «ሕዝቤ እውቀት ከማጣት የተነሳ ጠፍቷል»(ሆሴ 4፡6) ያለውን ልብ ልንል ይገባል፡፡ አምላኩን እንደሚገባ ያወቀ ሕዝብ ባወቀው መጠን ያመልከዋል፡፡ ይከተለዋል፡፡ ስለዚህ ምሰባኩ ላይ የሚቆሙ አገልጋዮች ማንነት፥ ቅድስና፥ዝግጅት ፥ ስጦታው፥ ችሎታው ሕዝቡን ለማነጽ ወሳኝ ነው፡፡

ሚሊዮን በለጠ

# መድረኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

## ማውጫ

መቅድም........................................................................................ 9

መግቢያ........................................................................................13

ክፍል አንድ መድረኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ.............16

1.1 በቃሉ የተፈጠረ አዲስ ሕብረተሰብ
1.2 ክርስቶስ የምስባኩ ማዕከል
1.3 የምስባኩ ተቀዳሚ ዓላማ
1.4 ምስባኩ ስቃሉ ተገዥ
1.5 በምስባኩ ስመቆም
1.6 ምስባኩ ስእነማን?
1.7 ምስባኩ እንዲዋብ
1.8 ምስባኩ እንዲጠበቅ

ክፍል ሁለት ትኩረት የሚሹ የመድረክ አገልግሎቶቻችን.........48

2.1 የመድረክ ትርጉምና ምንነት
2.2 የመድረክ ክብር
2.3 ፕሮግራም መሪዎችና መድረኮቻችን
2.4 ዘማሪያንና መድረኮቻችን
2.5 የቡድን ዘማሪያንና መድረኮቻችን
2.6 የሙዚቃ ቅንብርና መድረኮቻችን
2.7 ሰባኪያንና መድረኮቻችን
2.8 መባና መድረኮቻችን
2.9 ማስታወቂያዎችና መድረኮቻችን

ክፍል 3 የምስባክ (ፑልፒት) ኮሚቴ..................................107

3.1 የምስባክ ኮሚቴ ስምን?
3.2 ውጤታማ የምስባክ ኮሚቴ
3.3 የመጋቢው ሚና
3.4 የምስባክ ኮሚቴና የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ
3.5 የምስባክ ኮሚቴና ባለ እደራነት
3.6 የምስባክ ኮሚቴ እንደ ባስራእይ
3.7 የምስባክ ኮሚቴ እንደ ጠባቂ

ክፍል አራት የመእመኑ ምላሽ ለመድረኩ..........................140

4.1 ምእመኑ እንደ አምላኪ
4.2 ምእመኑ እንደ ተመጋቢ
4.3 ምእመኑ እንደ ተባባሪ
4.4 ምእመኑ እንደ ታራሚ
4.5 ምእምኑ እንደ ገምጋሚ
4.6 ምእመኑ እንደ ኃላፊ
4.7 ምእመኑ እንደ ጠያቂ

ማጠቃለያ

# ምስጋና

ከሁሉ በማስቀደም ይህቸን አነስተኛ መጽሐፍ ለመጻፍ ረድኤቱን ያበዛልኝን አምላክ እመስግናለሁኝ:: መንፈሳዊ ጽሁፍን ለማዘጋጀት ሲነሱ ከችሎታ ይልቅ ችሮታው÷ ከብልሃት ይልቅ ምሪት እንዲሁም ከጉልበት ይልቅ ረድኤት ተፈላጊ መሆኑን እንድማር ዕድል ስለ ሰጠኝ ምስጋና ይድረሰው:: ታየኝ የምለውን በእኔ ሁኔታ ለመግለጥ ባደረግሁት ጥረት የእኔነቱ አሻራ ያረፈባቸውን ጽሁፌቼን በትዕግስት አንብበው ገንቢ እርማት የሰጡኝን ወገኖች ጌታ አብዝቶ ይባርካቸው እላለሁኝ::

ወንድሜን ጋሽ ሚሊየን በለጠ አንዳስብ ያስገደዱኝን ጥያቄዎች በመጠየቅ እንዲሁም የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ አንብቦ ገንቢ አስተያየት ስለሰጠኝ አመስግናለሁኝ:: ፓስተር ሥዩም ገብረጻዲቅ ከድርብርብ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት እንዲሁም ከራሱ የዕረፍት ጊዜ ቆርሶ ረቂቁን አንብቦ ገንቢ ሃሳብ ስለ ሰጠኝና ስላበረታታኝ ጌታ ይባርከው::

ፓስተር ተስፋዬ ጋቢሶም እንደዚሁ ከድርብርብ የመጋቢነት ኃላፊነቱ ባሻገር የእኔን የጊዜ ገደብ አክብሮ÷ ጊዜ ውስዶ ረቂቁን አንብቦ ስለ ሰጠኝ ገንቢ ምላሽ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው:: በተጨማሪ ሞራሌን የሚገነባና በጽሁፍ ሥራ እንድገፋበት የሰጠኝን ወንድማዊ የአጋር ማበረታቻ ምንጊዜም አልረሳውም::

ወንድሜ ገዛኸኝ ሙሌ ጋሼ እያለ እያሞካሸ÷ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በተባ ብዕሩ የኔን የጎለደፈ ጽሁፍ ለማቃናት የበኩሉን ባያዋጣ ጽሁፌ ዛሬ የያዘውን መልክ አይዝም ነበር:: እርሱንም ጌታ ይባርከልኝ:: ወንድሜ ዶ/ር ግርማ ተስፋዬ ረቂቁን አንብቦ እያቸው ያለኝ ነገሮች በርግጥም ሊታዩ የሚገባቸው ነበሩ:: ወገኖች!! ቁጭ ብለን ስንወያይ የሰጠኝን ገንቢ ሃሳብ በምን



ልተምነው እችላለሁ? ጌታ ይባርክህ:: ወዳጄ ሰሎሞን ጥላሁን በበኩሉ ረቂቁን አንብቦ ግልጽነት የጎደላቸውን አባባሎች እሻሚ የሆኑ ነገሮችን ባያሳየኝ መጽሐፏ እንደ አሁኑ አትሆንም:: አህቴ ሰላም አስጥፋኖስም ረቂቁን በማረም ያደረገችው አስተዋጽኦ ታላቅ ነው ጌታ ይባርካት:: ወዳጄና የሙያ አጋሬ ውድነህ እንዳይላሉ ጥያቄየን በመመለስ÷ ይህች መጽሐፍ እንዲህ ዓይነት ቅርጽ እንዲኖራት የሰጠኝ ማበረታቻ የሚረሳ አይደለም::

የመጽሐፉን የሽፋን ስዕል ውብ አድርጎ ያዘጋጀውን ሰዓሊ መጋቢ ይድነቃቸው ለገሠን ከልብ እመስግናለሁኝ:: ከሺ ቃላት አንድ ስዕል የተበላውን እውነታ አስረግጦልኛል:: ጌታ ይባርከው:: በልፋታቸው ይህችን መጽሐፍ እዚህ ያደረሷትን ወገኖቼን ሁሉ ጌታ ይባርካቸው::

ስለ መጽሐፉ አስተያየት ቢኖራችሁ በፖ.ሣ.ቁ 101488 አዲስ አበባ ብላችሁ መጻፍ ትችላላችሁ::

ኃይሉ ቸርነት<br>
መሠረተ ክርስቶስ ኮሌጅ<br>
አዲስ አበባ

# መቅድም

ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን (1ቆሮ 14 ፥ 40)።

የምናመልከውና የምናገለግለው እግዚአብሔር አምላካችን የነፃነትና የሥርዓት እንዲሁም የዓይነትና የአንድነት አምላክ ነው። ስለዚህም የሁከት ሳይሆን የሰላም አምላክ ነው (1ቆሮ 14:33)። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን አበክሮ የሚያስገነዝበው ይህንን እውነት ነው። ለምን ቢባል፥ እነርሱ በነበራቸው የግል ሥጦታ ምናልባት በነጻነት የማገልገልን ጉዳይ ትልቅ ሥፍራ ሰጥተውት የመተሳሰብንና የመተናነጽን ጉዳይ ችላ ብለው ይሆናል። ሁሉም ዓይነት የጸጋ ስጦታ እያላቸው የአጠቃቀም ሥርዓትና የዓላማ አንድነት የጎደላቸው ይመስላል። በዚህ ምክንያት የጋራ በሆነ የማምለኪያና የመገልገያ ቦታቸው፥ መድረካቸው ሁሉን በአገባብና በሥርዓት ያደርጉ ዘንድ በጥብቅ እንደተመከሩ ማየት እንችላለን።

በተሰጠው ተራ በአገባቡና በሥርዓቱ እየቆመ፥ አገልጋይ የጠሰለና ኩልል ያለ መለኮታዊ መልእክት በሚናገርበት የአገልግሎት ቦታ እንግዳ ሰው ቢገባና ቢታዘብ ሊኖር የሚችለውን እዎንታዊ ምላሽ ሐዋርያው ጳውሎስ ጽፎልናል። ምላሹም በእውነት እግዚአብሔር በመካከላቸው ነው እያለ በፊቱ ወድቆ ለእግዚአብሔር መስገድ ነው (1ኛ ቆሮ 14:25)።

እግባብና ሥርዓት የጎደለው ያልታረመና ለመታረም ያልተዘጋጀ የመድረክ አገልግሎትን እንግዳ ሰው ቢያይ ፥ የሚሰማው የእግዚአብሔር ሕልውና ሳይሆን የአገልጋዮች የአሠራር ችግር ነው። እናም ወድቆ ለእግዚአብሔር መስገዱ ይቀርና ሌላ ጊዜ ወደዚያ ሥፍራ ላለመመለስ ወስኖ ሊሔድ ይችላል። በዚህ ዓይነት መንገድ እስከዛሬ የደረሰብንን የነፍስ ኪሳራ ለመገመት ይቻል ይሆን?

ስለ እርምት ስንነጋገር ግን በቁጥር ጥቂት ያይደሉትን በእግዚአብሔር ፍርሃትና በከፍተኛ የኃላፊነት ወይም የተጠያቂነት ስሜት ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ በማገልገል ላይ ያሉትን እየታረሙ ለመማር የተዘጋጅ ልብ ያላቸውን ቅን አገልጋዮች ማስታወስ ተገቢ ነው። ማስታወስ



ብቻ ሳይሆን በርቱ ማለትም ያስፈልጋል። በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት እንዴት መኖር እንደሚገባ ማወቅ ፥ የአገልግሎቱንም ክቡርነት መረዳት እየጨመረ እንዲሄድ፥ በምሳሌነታቸው የሚያስተምሩን ብዙ እሱንና እነርሱን እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካቸው እንላለን።

መቼም፥ የመስበኪያ ቦታ የእግዚአብሔር አፍ በተባሉ ሰዎች አማካይነት የእግዚአብሔር ክቡር ሃሳብ ወደ ሰው የሚተላለፍበት ክቡር ቦታ ነበር። ዛሬ በቦታው የሚቆሙት ሰዎች መሪ፥ ዘማሪ፥ አስተማሪ ወይም ሰባኪ ሊባሉ ይችላሉ። በዚህ ቦታ ግን እግዚአብሔርን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ፥ ለእግዚአብሔርም ሕዝብ ሕይወት በመጠንቀቅ ያገለገሉ ነቢያትና ሐዋርያት ነቀፋ የሌለውንና በክብር የሚታወስ ተልእኮአቸውን እየተወጡ እንዳለፉ ሊዘነጋ አይገባም። መድረኩ የጌታ ነው። ጌታን በምስባኩ ቆመን የምናገለግል ሁሉ ይህንን እንርሳ። ይልቁንም ለቃሉ አገልጋዮች ሁሉ ዋና አለቃና የአገልግሎቱ ባለቤት የሆነው ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቆመበት ቦታ መሆኑ ዘውትር ሊታወስ ይገባል።

በጋራ ለማምለክ በምንሰበሰብባቸው ቦታዎች ደግሞ ማረጋገጥ የሚገባን አንድ ትልቅ ጉዳይ አለ። ይህም እግዚአብሔርን ከልብ የማክበር ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር እንደ አባት የምንጠራውን ያህልና ጌታ እያልን የምንዘምርለትን ያህል ልባዊ የሆነ የአባትነት አክብሮትና የጌትነቱ ፍርሃት በእኛ ዘንድ ስለመገኘቱ ራሳችንን ሁልጊዜ መጠየቅ አለብን። በነቢዩ ሚልኪያስ የአገልግሎት ዘመን እንደነበሩት አይሁድ ቃላችንና አገልግሎታችን ከአፍ ያላለፈ፥ ወደ ልብ ጠልቆ በተግባር ያልተደገፈና የድፍረትም እንዳይሆንብን ቆም ብለን ማሰብ ይኖርብናል (ሚል 1፥6 ና 3፥ 13)።

አሁን አሁን በጉልህ ለሚታዩት የመድረክ ላይ ግድፈቶቻችን መሠረታዊ መነሻው ምናልባት እግዚአብሔርን አልፈራ ሰውንም አላፍር ብሎ ያመጸው ልባችን ሳይሆን ይቀራል? እግዚአብሔር ራሱ ምሕረቱን በእኛ ላይ ገልጦ የተፈራ ማንነቱንም ዳግም በማሳየት እርሞን የሚፈራ ልብ ይመልስልና!! ይሸለናልና።

ወንድማችን ኃይሉ ቸርነት መድረኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ በተሰኘ መጽሐፉ በዘመናችን በሰፋት እየተስተዋለ ላለው የጥንቃቄ ጉድለትና

እስከፊ ድፍረት ዓይነተኛ በሆነ የራሱ አቀራረብ እራሚ የሆነ ምክሩን ለመለገስ የበኩሱን ድርሻ እበርክቶእል የሚል እምነት እለው፥ የዚህ መቅድም ጸሐፊ:: ጠንክር አድርገን የአገልግሎታችንን አያያዝ መመርመር ሳለመድን ስእንዳንዶቻችን ሃሳቦቹ በአንዳንድ መልኩ ጠንክር ይሉብን ይሆናል:: ቢሆንም

«ጻድቅ በምሕረት ይገሥጸኝ፥ ይዝለፈኝም::

የኃጢአተኛ ዘይት ግን ራሴን አይቀባ፤ (መዝ 141፥ 5) ማለቱ ነው የሚያዋጣን:: ምክንያቱም በአገልግሎት አደባባይ ግራ የሚያጋባና ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ የሚያሳዝን ተግባር እየፈጸምን ሳለ የሰው እንደበት ከሚባርከን የአገልግሎቱ ዋናው ባለቤት፥ ጌታ፥ የሚልከውን ልኮ ቢያርመን ለነገ የምንተርፍ እንሆናለን:: ስለዚህ በሰፋና በለከነ እእምሮ የመጽሐፉን መልእክት ለመረዳት መሰናዳቱ ይመረጣል::

ይህ ማለት በገጾቹ ላይ የሰፈሩትን አረፍተ ነገሮች ሁሉ ለመቀበል ግዴታ እንገባለን ማለትም አይደለም:: የመጽሐፉ ደራሲም እንዲህ አይለንም:: ሃሳቦቹን በእግዚአብሔር ቃል እይታ የቤሪያ ሰዎች እንዳደረጉት «ነገሩ እንዲህ ይሆንን?» እያልን ብንመረምር ከደራሲው የልብ ትርታ ብዙ የራቅን አንሆንም ማስት ነው (የሐዋ 17÷11)::

ወንድም ኃይሉ በዚህ መጽሐፉ ፥ የምስባክ ኮሚቴንም ኃላፊነት በአጽንኦት ይጠቁማል:: ኮሚቴው የእረኝነት ሥራውን በትጋት እንዲወጣም በማሳሰብ ይጮኻል:: ይህ የእግዚአብሔር መድረክ የድረሱልኝ ጥሪም ይመስላል:: እዎን፥ ልዑል እግዚአብሔር በማዕካላዊነት ትኩረት ወለደ ሰላምና ጤና ለጪ እንዲሁም የሚያንጽ ድምጹ ሲሰማበት በሚገባው ምስባኩ ላይ ይህ ብቻ እንዲረጋገጥ ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ቸልታቸውን እቁመው ጥንቃቄ መጨመር ይኖርባቸዋል:: ባለማወቅ የሚያጠፉትን አስተምሮና መክሮ በማቅናት፥ ጀማሪ የመድረክ አገልጋዮችን በማለልጠንና በማበረታታት፥ የየዕለቱንም አገልግሎት ጊዜው ሳይረፍድ በመገምገምና እስፈላጊ ማስተካከያዎችን በማድረግ ትጋትን መጨመር የወቅቱ ብቻ ሳይሆን ወራትን ያስቆጠረ ጥያቄ ሳይሆን አይቀርም:: ስለዚህ---------------::

ሐዋርያው ጳውሎስ የእረኝነት ኃላፊነቱን ተወጥቷል:: የቆሮንቶስ ምእመናን በጸጋ ስጦታዎቻቸው በነጻነት እንዲጠቀሙበት እያበረታታ ሁሉ



ግን የእግዚአብሔርን ማኅበር፥ ቤተ ክርስቲያን በሚያንጽ መንገድ፥ በአግባብና በሥርዓት፥ ይሁን ብሏቸዋል:: ወንድም ኃይሉ ቸርነትም የዚህ ዘመን ኃላፊነቱን ለመወጣት ይህን መጽሐፍ አበርክቷል:: ቀሪው ድርሻና ምላሽ የእኛ የአንባቢያን በተለይም በእግዚአብሔር መድረክ ላይ መቆምን የምናዘወትረው ይሆናል:: በከበረውና በተቀደሰው የአገልግሎት ቦታ ላይ በማስተዋል እንድናገለግለው፥ በውጭ ያሉትን ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚያመጣ፥ የመጡትን ደግሞ በሰላም እያነጸ የሚያሳድግ መጽሐፍ ቅዱሳዊና መንፈሳዊ ሥራ እንድንሠራ ጌታ በጸጋው ይርዳን:: አሜን!!

ፓስተር ተስፋዬ ጋቢሶ
ከአዋሳ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን
መስከረም 7 ቀን 1997 ዓመተ ምህረት

# መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም ነገር የሚሆን ብርሃንን የሚለግስ መጽሐፍ ነው፡፡ በሕመም አልጋቸው ላይ ጋደም ብለው በደዌ የሚማቅቁትን ለማጽናናትና ለማበረታታት የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾችን ገለጥ አድርገን እንዲህ ይላል ብለን አጽናንተናል፥ መክረናል፥ አበረታትተናል፡፡ ደግሞ እንደ ሠርግ ባለ የደስታ ጊዜ ደግሞ ይህንኑ መጽሐፍ ይዘን አብሮ ስለ መኖር ከሚለግሰው ድንቅ ምክር ሙሽሮችንና ታዳሚዎችን መክረንበታል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ተሳስረን ስመኖር የሚረዳንን ደንብ ለማርቀቅ ስንፈልግም ይህንን መጽሐፍ ብንደገፍ የሚለግሰን ብርሃን አኩያ የለውም ብለን ከውስጡ በወጡ ሃሳቦች ደንባችንን ቀርጸናል፡፡ አንዳንዴም ከመስመር የወጣ ልምዳችንን መልክ አሲዘንበታል፡፡

የምንወዳቸውን ባጣንና በከፋን ጊዜ ደግሞ በልቅሶ ቤት ለሚያዝኑ መጽናናትን ከዚህ መጽሐፍ ያመጣንበት ጊዜ ጥቂት አይደለም፡፡ በተለይ ለቅሶ ቤት ይዘነው ስንቆም ደግሞ ይህ መጽሐፍ እዚህ ምን አመጣው? እዚያው ጸሎት ቤታቸው አይበቃም? እሁንስ አበዙት፥ እስከንባል ድረስ ላዘኑ ወገኖቻችን የሚበጅ ምክር፥ ለሐዘንተኞች የማጽናኚያን መልእክት ለማድረስ ከፍተነዋል፡፡ በየትኛውም የሕይወት ግስጋሴ ውስጥ ምክሩን ፈልገን ጠጋ ስንለው የሚረዳንን ጥበብ የሚያቀብል እንደዚህ ያለ መጽሐፍ የለም፡፡ አይኖርምም፡፡ ታዲያ ይህ መጽሐፍ ስለ መድረኮቻችንስ የሚለው ይኖር ይሆን? ብዬ ለአያሌ ወራት ቢሆን ጥያቄ ላስብ ቆየሁ፡፡ በእኔ መረዳት መድረኮቻችን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነትን የምናስተጋባበት፥ የእምላክን ፈቃድ የምናስታውቅበት ቦታ ናቸው፡፡

ምስባክ ጌታችን ልዩ ልዩ ባሪያዎቹን በመጠቀም ሃሳቡን ለማስተላለፍ የመረጠው ቦታ እንደሆነ ሁላችንም በደምላሳው የምናውቅ ይመስለኛል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አጠቃላይ ግንዛቤ ከመሪዎች ፥ ሰባኪዎች፥ መዘምራን እንዲሁም ከምእመናን እየራቀ በመድረኮቻችን ላይ የሚታዩ ነገሮች የማይጠበቁ እየሆኑ በመምጣታቸው ምናለ ብናስብበት? የሚል ልባዊ



ጥያቄዬን ጠይቄ ለመነሻ የሚሆኑ፥ ለእኔ የሚታዩኝን ጥቂት መፍትሄዎች ለማቅረብ ሙከራ አድርጌያለሁኝ፡፡ ዳሩ ግን እነዚህ መርሆዎች ያለቀላቸው፥ ፍጹምና የማይታረሙ ናቸው ብዬ አላምንም፡፡ ነገር ግን ቆም ብለን ራሳችንን እንድናይ ዕድል ይሰጡናል የሚል ግምት አለኝ፡፡

እኔና ይህንን እይታዬን የሚጋሩ ወገኖቼ ያለንበትን ሁኔታ ቆም ብለን በማየት ነገራችንን ለማረምና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ለማድረግ ካልተጋን ቅዱሳን አይታነጹም፥ ወንጌል አይሮጥም እንዲሁም ጌታ ያዝናል የሚል ድምዳሜ አለን፡፡ ስለዚህ ደግሞ መፍትሔው ለቤቱ ይገደናል የምንል ሁላችን ከምስባኩ (ከመስዊያው፥ ከፑልፒቱ ፥ ከመድረኩ) የሚፈስሰውና ለሕዝባችን የሚተላለፈው ነገር በመጽሐፍ ቅዱስዊ ቅርጽና ይዘት የተቃኘ እንዲሆን የበኩላችንን ስናዋጣ ነው፥ የሚል እምነት አለን፡፡

ይህች ትንሽ መጽሐፍ በዚህ አቅጣጫ ላለን ምኞት መነሻ የሚሆን ጥቂት ነገር ብላለች የሚል ግምት አለኝ፡፡ ከዚህ በኋላ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ጥልቀት ያላቸው ድንቅ ጽሁፎች፥ የጠለቁ ትምህርቶች እንዲገለጡና ምስባኮቻችን (መስዊያዎቻችን፥ ፑልፒቶቻችን፥ መድረኮቻችን ) ከሚታይባቸው ግዙፍ ጉድለቶች ነጻ ሆነው ሁላችንን እንዲያንጹ የሚያግዙ ድርጊቶች ይከናወናሉ የሚል ምኞትና ልባዊ ጸሎት አለኝ፡፡ አንባቢያን ጥቂት ክፍሎቿን አይተው ቅጽበታዊ እሉታዊ ምላሽ ከመስጠታቸው በፊት መጽሐፏን ከዳር እስከ ዳር በትእግስት እንዲያነቡ እጋብዛለሁኝ፡፡

በተጨማሪም ምስባኮቻችን ይህ መጽሐፍ እንደሚላቸው ናቸው? ወይስ ሌላ ገጽታ አላቸው? የሚለውን ጥያቄ በራስዎ እንዲመልሱ የተረጋጋ ጊዜ ወስደው ያስቡበት፡፡ መጽሐፏ የቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚቆሙትን፥ የሚያቆሙትን፥ ምስባኩ ላይ ከሚቆሙ የሚመጣውን የሚያስተናግዱ ተጋባዮቿን በየፊናቸው ቃኝታለች፡፡ ከዚያም በምስባኩ ላይ በሚቆሙት ወገኖች በህሉት ከፍላ ለማየት ትሞክራለች፡፡ ምስባኩ እዎንታዊም አሉታዊ ነገሮች ሲያስተናግድ አስተውላለችና፡፡ እንደ ቃሉ በሆነ የምስባክ አገልግሎት ታንጸናል ትላለች፡፡ በተቃራኒው ከቃሉ አፈነግጠ

በምንለው የምስባክ አገልግሎት ደግሞ አሞናል የሚል ድምዳሜዋን ለአንባቢያን ታቀርባለች።

ይሁን እንጂ እይታችን በሁሉም አቅጣጫ እንከንየለሽ ነው አትልም። ስለሆነም አንባቢያን በትእግስትና በጥሞና እንብበው ይበጃል የሚሉት እንዲታረም የሚፈልጉትን ነገር እንዲሏት ትጠብቃለች። የመጽሐፏ ትኩረት በቀዳሚነት እሁድ እሁድ የሚኖረን አምልኮ ጊዜ ላይ ነው። ትንታኔዋም የሚያጠነጥነው ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው በሚኖረው ጊዜ ላይ ነው። በተረፈ በአዘቦት ቀናት የሚኖረውንም የቅዱሳን ሕብረት እንስታ ምስባኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ እንዲቃኙ ማሳሰቢያ ታቀርባለች። እንግዲህ እኔ በዚህ ጥያቄ እንዳሰበ አንድ ግለሰብ የሚታየኝን ለማለት ምከሪያለሁኝ። ይህንን ጨምር ይህንን ደግሞ ቀንስ የምትሉኝን በልብ ስፋት ለማስተናገድ ሙሉ ለሙሉ ዝግጁ ነን። ጌታ ሁላችንም ፈቃዱን ፈጽመን ደስ እንድናሰኘው ይርዳን። መልካም ንባብ።

ኃይሉ ቸርነት
አዲስ አበባ መበከረም 1997



## ክፍል አንድ መድረኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

ጊዜው ብዙ ጥያቄ የሚጠይቅበት ነው። ጥያቄ በብዛት የሚጠይቅበት እንደዚህ ያለ ዘመን ከዚህ በፊት የታየ አይመስለኝም። በየአቅጣጫው ብዙ ጥያቄ ይጠየቃል። ጥያቄ የሚጠየቀው ግራ የሚያጋባ ድርጊት ሲፈጸም ነው። ለጥያቄ ተገቢ ምላሽ ሲጠፋ ሌላ ጥያቄ ይወለዳል። ያኔ የሕይወት እንግልት ይበዛል። የነፍስ ትግል ይጠነከራል። በተቃራኒው ለተጠየቀው ጥያቄ ደግሞ ሁነኛ መልስ ሲገኝ እረፍት ለጠያቂው ይሆንልታል። ለሕይወት ጥያቄ ተገቢ ምላሽን የሚሰጥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ መጽሐፍ የለም። ወደፊትም አይኖርም። መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም ነገር የሚሆን ብርሃንን የሚለግስ መጽሐፍ ነው።

መንፈሳዊ የሆነ ሁሉ ደግሞ ይህንን መጽሐፍ በመታዘዝ የውስጥ እምነቱን በውጫዊ ድርጊቱ ይገልጣል። የእግዚአብሔር መንፈስ በቃሉ ከተገለጠው እውነት ውጭ አይሠራም። ስለሆነም ከግላዊ ልምምድ ይልቅ በዘለቄታዊ ቃሉ የተመሠረተ ልማድ ምእመናን ያንጻል። ቃሉ እውነተኛ መተማመኛ ነው (መዝ 12:6 18:30 ምሳ30:5-6)። እንደ ቃሉ የሆነ አደራረግ በቅዱሳን መካከል ሲሰለጥን ጌታችንን ያስከብራል። ከቃሉ ውጭ የሆነ ነገር ሲያይል እኛን ያሰነቅፋል፥ የሚያመልኩት እንዴት ዓይነት አምላክ ነው? የሚል ጥያቄን ያስጠይቃል። ታዲያ በዚህ የጥያቄ ዘመን የሚያምነውም የማያምነውም ስለ መድረኮቻችን ይጠይቃል። የማያምኑት ሰዎች በጸሎት ቤቶቻችን በሚያዩት አግባብነትና ሥርዐት በጎዳላቸው ነገሮቻችን ምን ነካቸው? ብለው ሲጠይቁ ይስተዋላሉ። የወንጌል አማኞች ደግሞ ለመሆኑ መድረኮቻችን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚላቸው ናቸውን? የሚል ጥያቄን መጠየቅ ከጀመርን ዓመታት ተቆጠሩ። ሁላችንም የየበኩላችንን ጥያቄ እንጠይቃለን።

በጌታ ቤት የምንፈጽማቸው ተግባራዊ ድርጊቶች እንደ ሕያው ቃሉ መሆን ይኖርባቸዋል በሚለው አጠቃላይ መርህ ብዙ የወንጌል አማኞች ይስማማሉ። ስለሆነም ለሕብረት አምልኮአችንን የሆነ አደረጃጀት በመምረጥ መንፈሳዊ ድርጊቶቻችን እንፈጽማለን። የድርጊት ቅደም ተከተላችንን

የሚመራው የአደረጃጀት ቅርጽ እንደ ቤተ እምነቶቻችን ይለያያል:: ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ በብዙ ቤተ እምነቶች የአደራጃጀታችን ይዘቱ መሠረታዊ ልዩነት የለውም ። ምክንያቱም ለአደራረጋችን ሁላችንም ድጋፍ የምናደርገው ቃሉን ነውና:: በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ብንለያይም ስለ «አግባብና» ስለ «ሥርዐት» ያለን ልዩነት ያን ያህል የለፋ አይደለም:: በተለይ በወንጌላውያን ክርስቲያኖች ዘንድ እንዲህ ዓይነቱ ልዩነት በአገራችን ያን ያህል የጎላ አይደለም:: እንደውም አንዱ ቤተ እምነት ከሌላው ጋር ካለው መመሳሰል የተነሳ የልዩነት መስመር ማኖር አስከሚያስቸግር ደርሷል:: ስለሆነም ስለ መድረኮቻችን የሚነሳው ጥያቄ አብዛኞቻችንን ይመለከተናል::

መጽሐፍ ቅዱስ በቅዱሳን መካከል ያለው አምልኮ የሚያንጽና የሚገነባ እንዲሆን መመሪያን ይሰጣል:: ስለሆነም አደረጃጀታችን ሁላችንን የሚገነባና የሚያንጽ እንዲሆን «ሁሉም በአግባብና በሥርዐት ይሁን» ይለናል (1ኛቆሮ 14:40):: ከላይ በተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል ትዕዛዝ ላይ ሁለት መሠታዊ መርሆዎች ተቀምጠዋል:: በመድረክ ላይ ሕዝቡን ለማነጽ የሚፈስሱ ነገሮች በመጀመሪያ «አግባብነት» እንዳላቸው መጤን አለበት:: «አግባብ» የሚለው ነገር የአንድን ነገር መጥቀም ሳይሆን ትክክለኛ አደራረጉንና ቦታውን እንዲሁም የሚታይ ቅርጹን ይመለከታል:: በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በሕብረት አምልኮአቸው ሰዓት ሲፈጸሙ ስለሚገባቸው ድርጊቶች አግባብ ያለው አደራረግ ዝርዝር መመሪያ ሐዋርያው ጳውሎስ በ(1ኛ ቆሮ 11:2-16፤ 14:34-36) አስታወቀ::

በዚያ ማህበረ ሰብ ባሕሉ ተጠብቆ ስለሚከናወን ነገር ሐዋርያው ጳውሎስ መመሪያን ከላይ በተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይሰጣል:: በእነኚህ አማኞች መካከል እንዲደረጉ የታዘዙት ነገሮች አግባብነት ያላቸውና መፈጸም ያለባቸው ድርጊቶች ናቸው:: እነዚያ ድርጊቶች ከሕብረቱ አምልኮ አልተገኙም ማለት ትልቅ ነገር ጎደለ ማለት ነው:: ለምሳሌ «ሲጸልዩ መሸፋፈን» በዚያ ባሕል ተቀባይነት ያለው ድርጊት ነበር:: ስለሆነም አለመሸፋፈን አግባብ ያልሆነ ድርጊት ነበር:: ጸሎት ወይም ትንቢት ያለመሸፈን ሲከናወኑ ነውር መሆኑ ግልጽ ነበር::



በተጨማሪም ሴቶች መልእክት ሲተላለፍ «ዝም ይበሉ» ተባለ:: በዚያን ጊዜ ብዙ ሴቶች ያልተማሩ ስለ ነበሩ ከመድረክ የሚነገረውን ሁሉንም አይረዱም ነበር:: ስለሆነም ጥያቄ የሚሆንባቸው ነገር ሲኖር አጠገባቸው ያለውን ሰው ይጠይቁ ነበር:: የጉባኤም የመድረክም ንግግር በአንዱ ክፍለ ጊዜ መስተናገዱ የአምላኪውን ትኩረት በእጅጉ የሚያዛባ እንዲሁም የተናጋሪውን መንፈስ የሚረብሽ ጉዳይ ስለ ነበር «ሴቶቹ በጉባኤ ዝም ማለታቸውና» በቤት ባሎቻቸውን መጠየቅ አግባብ ነበር:: አግባብነት ያለው መመሪያ የተሰጠው አግባብ ያልሆነ ልምምድ ቤተ ክርስቲያኒቱን አናውጦ ስለ ነበር ነው:: «ዝም ይበሉ» የሚለው ትዕዛዝ የአገልግሎትን ሁነኛ አጋርና ግማሽ ክፍል ማፈን አልነበረም:: ይልቁንም የተሻለ አማራጭ ነበር:: ሁከት እንዲወገድ ይህን ማድረግ አግባብ ነበር::

ዛሬም አግባብነት ስላላቸው ነገሮች ስንነጋገር እንዲተኮር የምንፈልገው መድረኮቻችን ውበታቸው እንዲጨምር መደረግ ያለበትን እያደረግን መወገድ ያለበትን እንድናስወግድ ነው:: ምእመናን ገና ከቤታቸው «አግባብ» ያለው መሰናዶ አድርገው መምጣታቸው የመድረክን ውበት ይጨምራል:: ይሁንና ቤታቸው ጌታን እንደማያውቅ ሰው እየኖሩ በጸሎት ቤት ኃይማኖተኛ ቢሆኑ ጉባኤን ያስራሉ:: ስለሆነም አግባበነት ባለው መንገድ ሕይወትን መንከባከብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው::

አገልጋዮችም የጊዜው ቃል፥ የጊዜው መዝሙር፥ የጊዜው ሙዚቃ፥ የጊዜው የፍቅር ስጦታ፥ የጊዜው ማስታወቂያ በመድረኩ ጊዜያቸውን ጠብቀው በአግባቡ እንዲተላለፉ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸው እንደ ቃሉ የሚጠበቅባቸው መሆኑን ሲረሱት አይገባም:: ከላይ የተገለጹት መንፈሳዊ ድርጊቶች ከመድረኩ በጨዋነት ፥ በትአማኒነት ፥ በሐቅ፥ ራስን በመግዛት ወዘተ መተላለፋቸው ማረጋገጥ «አግባብነት» ያለው ድርጊት ነው:: እነዚህንና እነዚህን የሚመስሉ መንፈሳዊ አገልግሎቶች በአግባቡ ከመድረኩ ሲፈሱ እንታነጸለን::

በመድረኮቻችን «በአግባብ» እየሆኑ ያሉትን ጎሽ ብንል በመድረካችን ሲታዩ አይገባም «አግባብ» አይደሉም ብለን የምንላቸውን ደግሞ ይታረሙ ለማለት ይህ መጽሐፍ ቀርቧል:: ወገኖች!! በእኛም የዕለት ተዕለት ልምምድ

ስለ እነርሱ በሚነሳው ክፍል የተዘረዘረውን የመድረኩ ፈርጅ በጥሞና ማየት ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም በዝርዝር በቀጣይ ምዕራፎች ተጠቅሰዋልና ለዚያም ጊዜ ይበጡና ይዩት፡፡ ግርዶሹ እንዲወገድ ምን ማድረግ አለብን ለሚለው የተሰጠውን በትእግስት ይመልከቱና ያልተነካ ካለ ያክሉበት፡፡ ከዘማሪው ቀጥሎ በፕሮግራም ቅደም ተከተሉ የሚመጡት ሰባኪያን ለመድረኩ መታወክ የበኩላቸውን አዋጥተዋል፡፡ ሰባኪዎች በሥርዐት የሚናገሩ የቃሉ አገልጋይነታቸው በተግባር ለማሳየት አቅም ሲያንሳቸው ይስተዋላል፡፡ ስለሆነም ከቃሉ አገልጋይነት ዝቅ ብለው በመድረኩ የሚታዩ ጌታን የሸፈኑ ሰባኪያን አሉና እነርሱንም እንደ ዘማሪያኑ ጌታን የከለለውን ግርዶሽ እንዲያነሱ ጸሁፉ ያስገነዝባልና ጊዜ ለጥተው ይዩት፡፡

መድረኩ ላይ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚመጡ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለዛ ቢላበሱ ሁላችን እንታነጻለን፡፡ ስለሆነም ስለ መባና ማስታወቂያ እንዲሁም መድረኩ ላይ ስለምናከናውናቸው አያሌ ነገሮች በአግባብና በሥርዐት ሆነው ውበት እንዲጨምሩና እንደ ቃሉ እንዲሆኑ የቀረበውን ጥሪ በጥሞና እንይና ከቃሉ ጋር እናስተያያቸው ፡፡

በተጨማሪም ለአምልኮ የምንመጣና ከመድረኩ የሚፈስልንን የምንቀበል ምእመናንም ቤታችንን ማስተካከል ይጠበቅብናል፡፡ አገልጋዮች ከመድረክ የሚሰጡት አገልግሎት ውጤታማ የሚሆነው የምእመናን ልባዊ ተሳትፎ ሲጨመርበት መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ ሁላችንም ባቤታችን ጌታን ያለማቋረጥ ካልፈለግነው የሕብረት ጊዜ ትግል ይበዛበታል፡፡ አንዳንዶቻችን በቤታችን የምንኖረው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ኑሮ ከመድረኩ በሚፈበሰው አገልግሎት ላይ የራሱ ተጽእኖ እንደሚኖረው መዘንጋት የለበትም፡፡ ስለሆነም እኛም በአግባብና በሥርዐት እንኑር፡፡ ያለ ሥርዐት መሄዳችን አይበጅምና እንመለስ፡፡ እንዲሁም ለእርማት የተዘረዘሩ ሥርዐት ጎደል ድርጊቶችን ታግሳችሁ እንብቡኟቸው

የቀረቡት ማሳሳቢያዎች ከንቱ ወቀሳ ወይስ ጉድፋችንን እንለተን እንድንዋብ የተዘጋጀ መስታወት? የሚለውን ጥያቄ እናንተም ጠይቃችሁ የበኩላችሁን መልስ ለመስጠት ሙከራ አድርጉ፡፡ በማስከተልም ከእኔ ጋር መድረኮቻችን እንደ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲታዩ እንዴት ናቸው? በማለት ጠይቁ፡፡ ለራሳችሁ መልስ ስጡ፡፡ እኔ ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እዚሁ



ይገኛል፡፡ ለእኔ መጸሐፍ ቅዱስንና እነርሱን ሳስተያይ ታየኝ የምለው፡ በሚከተሉት ጥቂት ገጾች አቀርባለሁኝ፡፡ የእናንተ እይታና የእኔ ከተራራቀ ባልሁት ሁሉ ካልተስማማችሁ በመግቢያው በሰጧችሁ አድራሻ እንገናኝ፡፡ በምን መልኩ ያልኩት ሁሉ ፍጹም ነው አልልም፡፡ ግና መድረኮችን ሳያቸው መታረም እንዳለባቸው ይታየኛል፡፡ እንደኔ የበኩሉችሁን ለማዋጣት ተዘጋጁ፡፡ የሚያዋጣን በቃሉ መሠረት የሚከናወን አደራረግ ነውና (ቆላ 3፡16)፡፡

## 1.1 በቅዱስ ቃሉ የተፈጠረ ሕብረተሰብ

በሁለቱም የቅዱሳት መጻሕፍት ኪዳናት የእግዚአብሔር ሕዝብ የተገኘው ከቃሉ በኋላ ነው፡፡ በአዲስ ኪዳንም ይኸው እውነታ በተግባር ይታያል፡፡ ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን ዓላማና መጽሐፍ ቅዱስ ስንል ልናተኩር የምንፈልገው የክርበቶስ ሞትና ትንሳኤ ተሰብኮ እውን የሆነችውንና ጌታ በቃሉ አማካኝነት ዘወትር የሚያንጻትንና የሚያድሳትን አካሉን የሚመለከተውን እውነታ ማለታችን ነው፡፡ በሕያውና ሠራተኛ ቃሉ የተፈጠረችው ቤተ ክርስቲያን ከቃሉ አዋጅ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላት፡፡ በቃሉ ወደ ሕያውነት የመጣችው ቤተ ክርስቲያን በሕያውነት እንድትቀጥል እግዚአብሔር ቃሉን በመጠቀም ያጸዳታል፣ ይቀድሳታል እንዲሁም ያድሳታል፡፡ (ኤፌ 5፡26-33)

ቤተ ክርስተያን በቃሉ ያለ ማቋረጥ መደገፍ አለባት የሚለው መረዳት በሁሉም ክርስቲያኖች ዘንድ አይገኝም፡፡ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክርስቲያን የቃሉ ደራሲ ናት ብለው ስለሚያምኑና ስለሚያስተምሩ ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ላይ ሥልጣን እንዳላትና አድራጊ ፈጣሪ እንደሆነች አድርገው ያቀርባሉ፡፡ እርግጥ ነው፣ በሁለቱም ኪዳኖች መጽሐፉ የተጻፈው በቀጥታ ለሚያምነው ህብረተሰብ ነው ፡፡ ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ተፈጠረች እንጂ ቃሉን አልፈጠረችውም፡፡[1]

[1] Hailu Cherenet Hiyaw Kibibil Addis Ababa: Commercial Printing Press, 2003.

ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን በሕያውነት የምትኖር እንዲሁም ተልእኮዋ የማያቋርጥ ኃይል ያለው እንዲሆን ለቃሉ ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንዳለባት መገንዘብ ያስፈልጋታል:: ምክንያቱም ቃሉን ቸል ስትል ወደ ድንቁርና እና ወደ ሞት ታዘግማለችና ነው:: ቃሉን እንደሚገባ በምታውጅ ቤተ ክርስቲያን ባለ ራእዮች በሙላት ይታያሉ::[2] አባሎቿም በጎ ተጽእኖን የሚፈጥሩ የአዲሱ ህብረተሰብ አባላት ሆነው ለሚኖሩበት ማኅበረሰብ ጨውና ብርሃን በመሆን ያገለግላሉ:: የእምላክ ፍቅር ለሰዎች በተግባር ይታያል:: ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው እውነተኛውን እረፍት ይለማመዳሉ:: ምክንያቱም እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል የሚፈስሰውን የፍቅር ፥ የመታዘዝና የመከባበር ግንኙነት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው በተግባር ለማሳየት በክርስቶስ ፍቅር የተሳሰሩ የአማኞች ስብስብ ናትና::

ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረት በቀደምትነት የተላኩት የእምነት አባቶች እጥቢያዊ ማንነትን እንድትላበስ የአካባቢውን መጠሪያ ለቤተ ክርስቲያን በመስጠት ተጠቀሙ:: የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ 8:1) ፥የእስያ ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ 16:5) ፥ የሮም ቤተ ክርስቲያን (ሮሜ 16:5) ወዘተ.. ማለትን መረጡ:: የቤተክርስቲያን ሕልውና እንዲቀጥል መንፈሳዊ ትምህርትን ቀዳሚ ሥራቸው አደረጉ::

- ❖ ከተረት የጸዳ ኑሮ (1ኛ ጢሞ 1:3-5)
- ❖ እግዚአብሔርን መምሰል (1ኛጢሞ 4:6)
- ❖ እውነተኛ መንፈሳዊ ርምጃ (1ኛ ጢሞ 6:17)

ወደ ሕብረቱ የሚቀላቀሉትም ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት እንዲመሩ ትኩረት ይደረግ ነበር:: ስለሆነም ቤተክርስቲያን የጸጥታ ሥፍራ፥ የሰላም መቅደስ፥ የጥርጣሬ መጥፊያ፥ የመጽናናት ሥፍራ፥ የተስፋ ማደያ፥ የጸሎት ሥፍራ እንዲሁም የማምለኪያ ቦታ ሆኗ እንድትቀጥል የምትኖረው ቃሉን ለማወጅና እንደ ቃሉ የሆነ ሕይወት በተግባር እንዲታይ መሆኑን መገንዘብ

---
[2] Ibid



ያሻታል:: መድረኳ ይህንን እውነታ በጉልህ ማስተጋባት ይኖርባቸዋል:: ዋና ዓላማዋም ቃሉን በማወጅ የእምላክ መንግስት እንዲሰፋ ክብሩ እንዲሰራፋ ማድረግ ነውና::

የውይይት ጥያቄዎች

1. በእናንተ እይታ ቤተ ክርስቲያንን ያስገኘው ቃሉ ነው ወይስ ቃሉን ያስገኘች ቤተክርስቲያን ናት?
2. ቤተ ክርስቲያን በሕያውነት እንድትቀጥል ቃሉን ማወጅ ይኖርባታል ስንል ምን ማለታችን ነው?

## 1.2 ክርስቶስ የምስባኩ ማዕክል (ቆላ 3:16-17)

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ከእርሱ ትምህርትና የመሥዋዕትነት ሥራ የተነሳ የተሳሰሩ አማኞች የእርሱን ፈለግ ተከትለው እርሱን በሕይወታቸው በመግለጥ ሌሎችን ወደዚህ ሕብረት ለመጥራት እንዲችሉ ነው:: ቤተ ክርስቲያንም በመድረኳ ይህ ተቀዳሚ ዓላማ የሚተገበርበት ማንኛውም ነገር እንዲከናወን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይኖርባታል:: በመድረኩ ላይ የሚከናወነውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ የሚገዛው ይህ አውራ ሃሳብ ሲሆን ይገባል:: በመከከላችን እሱ ከፍ ያለ እንደሆነ እርሱ ሁሉን ወደ እርሱ የሚስበሰብበት ልዩ ሁኔታ ይፈጠራል:: ክፉ ከሆነው ከዚህ ዓለም ያዳነንን፥ መልካሙን ሥራ እኛን ሆኖ ያከናወነልንን ጌታ በጉባኤያችን ለማምለክ ወይም ለማወደስ እያንዳንዱ ድርጊት ከዚህ አውራ ዓላማ ዙሪያ መቃኘት አለበት::

መጽሐፍ ቅዱስ «የጌታ መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ» (2ኛ ቆሮ 3:17) ይላል:: በቤተ ክርስቲያን ምስባክ ላይ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚስተናገዱ፥ የትልቁ ዓላማ ክፍሎች የሆኑ ፕሮግራሞች በሙሉ ፥ ፍስታቸውን ጠብቀው አንድን እውነት ለመግለጽ በአንድ ድምጽ ማስተጋባት አለባቸው:: ያም ድምጽ «ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ከፍ ሊል ይገባዋል» የሚል መሆን አለበት:: ቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነላትን ጌታ ሕይወት በልዩ ልዩ የአካል ክፍሎቿ እንቅስቃሴ በተግባርና በተጨባጭ ልታሳይ ይገባልና::

ክርስቶስን ከመድረኮቿ ከፍ አድርጋ ማሳየት የተሳናት የእርሱን ቃል ለማስተጋባት አቅም ያነሳት ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል ናት ለማለት ያስቸግራል:: ከእድር ከዕቁብና ከሙያ ማኅበር መድረኮች የተለየ መድረክ ቤተ ክርስቲያን አላት ብለው አገልጋዮቿም ሊናገሩ ሲያጎሉ የሚፈልጉት ክርስቶስ የእንቅስቃሴው ቁንጮ እንዲሁም የድርጊቶች ሁሉ አውራ መሆኑን ከመድረኮቿ በማስተጋባታቸው ነው:: ከላይ በጠቀስናቸው ትስስሮች መያያዝ አለ:: ከእድር ፥ ከዕቁብና ከሙያ ማኅበር ጋር ባለው መያያዝ ገዝፎ የሚታየው ጥቅምና መደጋገፍ ሊሆን ፥ ልዩነቱ የቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚታየው መያያዝ የሕይወት ለሕይወት የሆነ ግንኙነት የቀደመበት መተሳሰር ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የተሰጠው መሆኑ ነው::

ክርስቶስ መልኩን እንዲያንጸባርቁለት ዛሬ በዚህች ዓለም የተወው ከእርሱ የተነሳ የተሳሰሩትን አማኞች ነው:: እነርሱም መድረካቸውን ለሌላ ነገር አሳልፈው ከሰጡበት በቤቱ መብቱን የተቀማ ሐዘንተኛ ይሆናል:: እርሱ እንዳያዝን ቤተ ክርስቲያን እርሱን ማዕከል ያደረገ የአገልግሎት እንቅስቃሴ ሊኖራት ይገባል:: እርግጥ ነው አማኞች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ጌታ የሚያንጸባርቅ አካሔድ በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል:: ይሁን እንጂ በጸሎት ቤት እሱን እነሰማለን ብለው ተሰብስበው ትኩረትን ከእርሱ ወደ ልዩ ልዩ ነገሮች የሚወስድ ሁኔታ ሊፈጠር ጌታ ደስ አይለኝም:: ስለሆነም ለመጸሰይ እንደበታቸውን የሚከፍቱ መሪዎች ፥ በዜማ መልእክት ለማቅረብ የታደሙ ዘማሪያን ፥ የዕለቱን መልእክት ለማቅረብ የተሰናዱ ሰባኪያን እንዲሁም ታዳሚዎች የጌታ ስሙ እንዲቀደስ፥ ክብሩ እንዲወደስ በየፊናቸው ተልእኮአቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል::

በአባላት የስብሰባ ጊዜ ሪፓርት ቀርቦ በጠንካራና ደካማ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አካሔድ መነጋገር ስሀተትነት ባይኖረውም በመደበኛ የአምልኮ ጊዜ ላይ ግን የቤተ ክርስቲያን መድረኮች ለክስና ለአሉባልታ የተከፈተ በር ሊኖራቸው አይገባም:: በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን መድረኮች እሮሮና አምባጓሮ ለማስተናገድ የተመቻቹ መሆን የለባቸውም:: እንዲሁም ከሁነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያፈነገጡ አስተሳሰቦችና አደራረጎችን ለመሸከም መፍቀድ የለባቸውም:: መድረኩ የአምላክ ፥ ቤተክርስቲያንም ይህንን የአምላክ



ንብረት በአደራ ልታስዳድር የተሾመች ወኪል መሆኗ ለአፍታም እንኳን መዘንጋት የለበትም:: መድረክ በእንዲህ ዓይነት ቅዱስ ፍርሃት በክብር ሊያዝ ይገባዋል:: ይህንን ስንል ለመድረኩ ያለን የተጋነነ አክብሮት የአምላክን ቦታ እንዳይወስድ መጠንቀቅ አለብን:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ንጉሥ ሰሎሞን ሕዝቡ አምላኩን የሚፈልግበት ሥፍራ ለማዘጋጀት በአባቱ በዳዊት በእግዚአብሔርም ተመረጠ:: የተሰጠውን አደራ በመፈጸም ግንባታውን ካጠናቀቀ በኋላ አምላክን ወደዚህ ማደሪያ እንደዲመለከት በብዙ ፍርሃት ተማጠነ:: እግዚአብሔርም በተለየ መንገድ መጥቶ ለዚህ ልመና እሺታውን በገሃድ አሳየ (1ኛ ነገ 8:11)::

ሕዝቡም እግዚአብሔር በሚታወቃቸው መንገድ በመካከላቸው ስለተገኘ ሐሤት አደረጉ (1ኛነገ 8:67):: ይሁን እንጂ አምላካቸውን ትተው ቦታውን ማምለክ ሲጀምሩ ከብሬ ይኖርበታል፥ ለዘለቄታውም በዚያ እሆንበታለሁ ያለውን ቤት ተወው:: ሕያዉን ጌታ ትተው በድኑን ሕንጸ የሙጥኝ ሊሉ፥ የአምላክን ያህል ክብርም ሊሰጡት ጌታ ተቆጣ:: አላፊ ከሆነው ነገር የተሰራውን መቅደስ ብቻ በማክበር የዘላለሙን ጌታ ገሸሽ አደረጉት:: በዚህ ጊዜ ነገር መስመሩን ሲለቅ የቃል ኪዳኑ ሕዝብ ጠላቶችም መጥተው እንዲያፈርሱት ፈቀደላቸው:: ከሚታይው ወደ ማይታየው፥ ከእሁኑ ይልቅ ዘለቄታውን እንዲያዩ ፈልጎአልና:: እኛም ዛሬ አምላካችን በድርጊቶቻችን ቢገለጥ እሱን ትተን ድርጊቶችን ከእርሱ በላቀ ሁኔታ ከፍ ከፍ ብናደርግ ከፍተኛውን ስህተት እንፈጽማለን:: ሳምራውያን ገሪዛን በሚባል ተራራ እግዚአብሔር በተለየ መንገድ ተገልጦ ያከናወነውን ታሪክ ያስታውሳሉ:: ይህንንም ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው አስተላልፈዋል:: ይሁን እንጂ ዘመን እልፎ ዘመን ሲተካ በተራራው ላይ ለየት ባለ መንገድ የተገለጠውን የሰማይ አምላክ ትተው ተራራውን የሙጥኝ አሉት::

እኛም ዛሬ አንድ መዝሙር ስንዘምር በተለየ መንገድ ብንባረክ ነገ ቀመልሰን ያቺኑ መዝሙር የሙጥኝ ማለት ይቃጣናል:: የባረከን መዝሙሩን ተጠቅሞ እኛን የነካን አምላካችን እንጂ መዝሙሩ በውስጡ የተለየ ነገር ስላለው አይደለም:: ምስባኩን ልንጠነቀቅለት ይገባል ስንልም እናምልከው ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል:: ይሁን እንጂ እንደ ተራ ሥፍራ ልናየው ደግሞ አይገባንም:: መድረክ የተከበረ የአምላክ መገለጫ ሥፍራ ነውና::

በአደባባይ የሚቀበል የትኛውም አገልጋይ የውስጣዊ ሕይወቱ መገለጫዎች በጥብቅ መታየት አለባቸው፡፡ ስለዚህ ግላዊ ሕይወትን፥ ቤተሰባዊ ሕይወትን፥ ከሌሎች ጋር ያለ ግንኙነትን እንዲሁም ማኅበረሰባዊ ሕይወትን ጠጋ ብሎ በመመልከት የምሰባኩን አደራ መስጠት ለቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ለሚያገለግሏትም ይበጃል ፡፡

በእንዲህ ዓይነቱ ፈታኝ ጎዳና ተጉዘው አደራን የሚቀበሉ አገልጋዮች የአገልግሎት ዘመን ይረዝማል፡፡ እነርሱም በብስለት በምሳሌነት ለማደግ ዕድል ያገኛሉ፡፡ በአሁን ጊዜ በብዙ ሥፍራ የሚታዩ አገልጋዮች ጠዋት ተሰቅሎ ማታ እንዳሚወርድ ሰንደቅ ዓላማ ለጥቂት ጊዜ ታይተው ከመድረኮቻችን ወዲያውኑ ይጠፋሉ፡፡ ዛሬ ዛሬ ብልጭ ብለው ድርግም የሚሉ አገልጋዮች በዝተዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት ተገቢው ፍተሻ ሳይደረግ አደራ ይሰጥና እውነተኛ ማንነታቸው ሲገለጥ «ቤተ ክርስቲያንንም ለማዳን ለአገልጋዩ ጥንቃቄ ለማድረግ በሚል ሰበብ ገለል» ሲደረጉ ይስተዋላል፡፡ ሞራላዊ አቋማቸው የሚነቀፍ ሆኖ ይህንን ማድረጉ ምንም ስህተትነት የለውም፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱን ርምጃ በመደጋገም ግለሰቦችን ከመጉዳት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ያልተፈለገ ችግርን ከመደንቀር ይፋዊ አድራን የሚቀበሉ አገልጋዮችን በብዙ ጥንቃቄ መመልመሉ ያዋጣል፡፡ ስለሆነም የአደባባይ አደራን ከመስጠት በፊት ቅደመ ፍተሻ ላይ ጠንቃቃ አሠራርን ማጎልበት ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለግለሰቦቹ የሚበጅ ነገርን እንዲለመድ ያደርጋል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ጥንቃቄ ይፋዊ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አገልጋዮች ሁሉ አይዘነጉትም፡፡ ስለሆነም በሚከተሉት ሁኔታዎች ምስባኩ ላይ መቆም ያላበቸውን ሰዎች መለየት አለባቸው፡፡ ምስባኩ ላይ የሚቆም ግለሰብ በሞራላዊ አቋሙ መነቀፍ የለበትም፡፡ ለምሳሌ ምስባኩ ላይ የሚቆም ትዳር ያለው ከሆነ የተመሰከረለት ያንድ ሚስት ባል መሆን ይኖርበታል፡፡ ላጤ ከሆነ ደግሞ አጠራጣሪ ጾታዊ ግንኙነት ያለው መሆን የለበትም፡፡ ብዙዎች ጣታቸውን የሚቀስሩበት የሚነቀፍ ሞራላዊ አቋም ያለውን ሰው ወደ እንደዚህ ዓይነቱ አካባቢ ማምጣት እርሱን ማሳጣት ቤተ ክርስቲያንንም ማስነቀፍ ይሆናልና መጠንቀቁ ይበጃል፡፡



ስለሆነም እነዚህ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ባህሪያት በምስባኩ ላይ የሚቆመውን አገልጋይ ለሞራላዊ ጥንካሬው በሚበጅው ባህሪ ተገንብቶ እንደሆነ እና እንዳልሆነ ለማየት ለሚያግዙት ራሱን ቢያይባቸው ይረዱታል፡፡ ስለሆነም አገልጋዮች በመጀመሪያ እነርሱነታቸውን በተመለከተ ራሳቸውን የሚገዙ ፥ እንደሚገባቸው የሚሠሩ ፥ የማይነቀፉ፥ ልከኞችና በቃልም ሆነ በኑሮ ሌሎቹን ለማስተማር የሚበቁ ቢሆኑ በሚቆሙበት መድረክ ሞገስ ያላቸው ይሆናሉ፡፡ መድረክ ላይ ስንቆም የምንታየው እኛ ብቻ እንደሆንን ካሰብን እራሳችንን እናታልላለን፡፡ እኛና ከእኛ ኋላ ያሉት ቤተሰቦቻችንና ጓደኞቻችን ይታያሉ፡፡ እኛ ሁሉንም ለማየት የታደልነውን ያህል ሁሉም ፊታቸው የቆምነውን እኛን ብቻ ሳይሆን ከእኛ በስተኋላ ያለውን አበጥረው ያያሉ፡፡

ስለሆነም የእኛን ብቻ ሳይሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ቤተሰባዊ ሕይወታችንን በተመለከተ ማስተዋል የሞላበት አካሔድ ሊኖረን ይገባል፡፡ ወላጆች ከሆንን ልጆቻችን የእኛን እምነት የሚያከብሩ፥ ፈለጋችንን የሚከተሉ ሆነው መታየት አለባቸው፡፡ አሊያ ቤታችን ያልሠራውን መድኀኒት ለማዘዝ ምስባኩ ላይ ብንቆም ለሚፈርዱብን ሰዎች ራሳችንን አሳልፈን እንሰጣለን፡፡ ቤተሰቦቻችን የኛን ሕይወት የሚቀበሉ የውጤታማ መንፈሳዊ አመራራችን የተግባር ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ ይህ ካልሆነልን በቤታችን አሸንፎ ያልወጣን እውነት በአደባባይ ለመናገር አቅም እናጣለን፡፡ በዚህ አቅጣጫ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ያየናቸው አያሌ ቅዱሳን ተፈትነዋል፡፡ ዛሬም ይህ ፈተና እውን ነው፡፡ ልጆቻችን የማሳመን ችሎታና በግድ የኛን ፈለግ እንዲከተሉ ማድረግ አንችልም፡፡ ይሁንና በቂ ትኩረት ሰጥተን ጌታን ጌታቸው አድርገው እንዲኖሩ የበኩላችንን ማዋጣት አለብን፡፡ በተጨማሪም በአገልግሎታችን ላይ ጥቁር ጥላ እንዳይወድቅና እኛንም የማገልገል ነጻነት እንዳይነሳን የማያቋርጥ የምልጃ ጸሎት ያስፈልገናል፡፡

ምዕመናንም የመድረክ አገልጋዮች ከጠላት ጋር በሚደረግ ፍልሚያ ግምባር ቀደም ግብ ግብ በመግጠም ላይ እንዳሉ ተገንዝበው ሊማልዱላቸው ይገባል፡፡ በመድረክ አገልጋዮች ገንቢ አስተዋጽኦ የታነጽን ሁላችን እነዚህ በመድረክ ላይ ግምባር ቀደም ሚና በመጫወት የሚጠቅሙን አገልጋዮች

ቁልፍ የአመራር ቦታ ላይ እንዲመጣ እንዲህ ዓይነቱን ግለሰብ መገፋፋት እንደማይበጅ ተገንዝበን መታቀብ አለብን ::

በጌታ ያልቆየ ግለሰብ ከቆይታው ጋር የማይመጣጠን ታላቅ ኃላፊነት ስንሰጠው በትዕቢት ተሞልቶ እንዳይሰናከል ወደ መድረክ ከመውጣቱ በፊት በቂ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል። ምክንያቱም መቻከል የበዛበት ጉዞውና በፍጥነት የደረሰበት ቁልፍ የመድረክ ቦታ ስለማንነቱ የበለጠ በትዕቢት እንዲያስብ ስለሚገፋፋው አዲስ አማኝ የቱንም ያህል የተዋጣለት ቢሆን ወደ እንደዚህ ዓይነቱ ከፍተኛ የኃላፊነት ሥፍራን በተቻኮለ ሁኔታ ልናመጣው አይገባንም። ይልቁንም ጊዜ ወስዶ ለታማኝ አገልጋይ የሚጠቅሙ ባህሪያትን እንዲገነባ ዕድል ልንፈጥርለት ይገባል። ይህንን ማድረግ ለግለሰቡም ለቤተክርስቲያንም ጠቃሚ ነው::

## ሴ. ምስባኩ ላይ መቆም ያለባቸው በመንፈሳዊ ስጦታቸው የተመሰከረላቸው መሆን አለባቸው

በምስባኩ መቆም ያለበት በመጀመሪያ በንጽህናው የተመሰከረለት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ስጦታው እንዳለው ያረጋገጠ ሌሎችም ያረጋገጡለት ሰው መሆን አለበት። ልምምድ ለአማኞች መብሰልና ለኃላፊነት መብቃት አስተዋጽኦው ቀላል ባይሆንም መንፈሳዊ አገልግሎት በኩረጃ ወይም በልምምድ ብዛት አይከናወንም። ሰው በልምምድ ትንቢት እንደማይናገር ሁሉ በልምምድም የመድረክ አገልጋይ አይሆንም። እዚህ መባል የተፈለገው ልምምድ ጠቃሚ አይደለም ሳይሆን ልምምድ የስጦታ ምንጭ አይደለም። ልምምድ ስጦታን ያጎለብታል። ይሁን እንጂ ባለስጦታ አያደርግም።

ብዙ ጊዜ «በመገለጥ ይመጣሉ» ስለሚባሉ ነገሮች ያለን አመለካከት ቅጽበታዊና ተአምራዊ ነው። ተአምራዊ ብለን የተቀበልናቸውም የሰው ጥልቀት ያላው አሳቤ ሳይገባባቸው ድንገት በመሆናቸው ነው። ጊዜ ፈጅተው በአገልጋይ ሕይወት የሚፈጸሙትን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ግን መንፈሳዊ ስጦታ ቢሆኑም እንኳን በልምምድ እንደሚደረስባቸው እናስባለን። ጊዜ ከሚወስዱ መንፈሳዊ አገልግሎቶች መሐል ዝማሬና ስብከት ይገኙበታል። አገልግሎቱ ሲሰጠን ቅደም ተከተል ጠብቀን ሲያስፈልግም ማስታወሻ ይዘን መልእክት እናስተላልፋለን። ያንን አደራረግ ተአምራዊ ብለን መጥራት



አንፈልግም። የተዋበ ድምጽ የሰው ሥሪት አይደለም። ነገር ለሰው በሚገባ መግለጽ በምርጫና በልምምድ አይገኝም የጌታን ረድኤት ይጠይቃል። ጊዜ ወስደን የምናስተላልፈው መንፈሳዊ አገልግሎት በልምምድና በጥረት ብቻ እንደሚገኙ ብቻ ማሰብ ስህተት ነው። ለእነርሱም የጌታ ረድኤት እንደሚያስፈልግ እንረዳ። በመድረክ ቆመው ጌታ የሚናገረኝ እናገራለሁ ለሚሉን ብቻ የጌታ ሌሎችን ግን የፍጡር ማድረግ ይቅርብን።

ያለ ዝግጅት በቅጽበት የሚመጡትን መለኮታዊ ለንላቸው አንዳንድ የመድረክ አገልግሎቶችን ግን ለአዝጋሚ ልምምድ አንሰጣቸዋለን። ይህም የመድረክ አገልግሎቶችን ትክክለኛ ተፈጥሮአቸውን መካድ፥ ምንጫቸውንም ማራከስ ስለሆነ በውል ሊጤን ይገባል። የሁለቱም ምንጭ አምላክ ከሆነ ቅጽበታዊም ሆነ አዝጋሚ ስጦታዎችን በማበላለጥ ማየት የለብንም። ቀደም ብለን እንደተነጋገርን በልምምድ መገለጥ እንደማይመጣ በልምምድ ብዛት የመድረክ አገልጋይ አይኮንም። ጊዜ ለብስለታችን የሚያዋጣው ነገር ቢኖርም ጊዜ ግን የስጦታ ምንጭ አይደለም።

ስለሆነም በምስባኩ ላይ ስለሚቆሙ ሰዎች ስናስብ ስጦታው ያላቸው መሆን ያለባቸው መሆኑ ለድርድር አይቀርብም። ስጦታው የሌለው መድረክ ላይ መቆም የለበትም። ያለው ደግሞ መድረኩን መነፈግ አይኖርበትም። ያለውን ትቶ የሌለውን ማሰማራት ከመስመር ለወጣ ሰይጣናዊ አሠራር ራስን መስጠት ነው። በአካል ውስጥ ያሉ ብልቶቻችንን አገልግሎትና የሥራ አፈጻጸም በተመለከተ ስናስብ ሁላችንም ግልጽ የሚሆንልን ነገር አንዱ እንዱን ተክቶ ሥራውን መፈጸም አለመቻሉን ነው። አንዱ ብልት ሌላውን ሆኖ ሥራ ማከናወን እንደማይሆንለት ያለብዙ መግለጫ ይገባናል። ልክ እንዲሁ የመድረክ ስጦታ የሌለው ግለሰብ በመድረክ ላይ ይሳከለታል ብሎ ማሰብም ሞኝነት ነው። ይሁን እንጂ በመድረኮቻችን ጸጋው የሌላቸው ሰዎች ቆመው እነርሱ ያለ ኃፍረት በሚፈጽሙት ስህተት ጉባኤው ትርምስምስ ሲል ማየት ብዙዎቻችንን አያሳቅቀንም። እንደውም ደግመን ደጋግመን በመጋበዝ ያንኑ ጉድለታቸውን በአደባባይ እንዲደጋግሙ ዕድል እንሰጣቸዋለን።

ከአውቀት ማነስ የተነሳ በምንፈጥረው ስህተት እንዳንቀጥል አምላክ ትዕግስቱንና ርህራሄውን ለእኛ በማብዛት ተምረን እውነትን እንድረዳና

አይመልሳቸው። በዚህም ድርጊታቸው ሁኔታዎችን በጽሞና መከታተል ለሚወድ ሰው ያልተፈለገ ሥራ ይሰጡታል። ጌታን ሊያመልክ በመጣበት በታ የትዝብት መድረክ ይከፍቱለታል። መሪዎች እንዲህ ያለውን ጥንቃቄ የጎደለው አደራረግ ቢያስወግዱ ለአዳማጭም ለተመልካች የሚበጅ ነገር ተከናውኖ አምልኮውም ይሳካል። አለበለዚያ ከአምላኪው ከፊሉን ሳይወድ በግድ ወደ ታዛቢነትና ገምጋሚነት ሥራ ውስጥ ይገባል። ይህ ደግሞ ትልቅ ጉዳት ነው። ማስተዋል ከጎደለው አደራረግ የተነሳ ለምን ሰዎችን እናጣለን? ለምንስ ሰዎችን ወዳልተፈለገ መስመር እንነዳለን?

## የሚያስለች ድርጊት መፈጸም (ምሳሌ 30:33)

አምልኮን አታካች ከማድረግ የከፋ ድርጊት በሰንበት ቀን አይኖርም። አያሌ ሰዎች ወደ ጸሎት ቤት የሚመጡት በጉጉት ነው። ያንን ጉጉታቸውን ከሚቀንሱ ድርጊቶች መካከል አዝማቾችን በሚያሰለች መንገድ እየደጋገሙ ሰዉ እስኪደከመው መዘመር ነው። ሰዉ መሰላቸቱን ለመግለጽ የተለያዩ ድርጊቶች ይፈጽማል። ቆሞ ከሆነ ይቀመጣል። ቁጭ ብሎም ከሆነ ያዛጋል፤ ወይም ሰዓቱን አሥሬ ያያል። እኛ ግን እንደ መሪ ሕዝቡን ስለማናነብ ወይም በድርጊት ምላሹ በለምንቆጣ ሕዝቡ የሚሰላችበትን ነገር በማድረግ ለመበቀል እንሞክራለን። አንዳንዴ ሕዝቡ በግድ እንዲያጨበጭብ ሌላ ጊዜ «አንድ ሰው እንዳይቀመጥ» በሚል ማስጠንቀቂያ ፈቃዳችንን እንዲፈጽም እናስገድዳለን። እንቀመጥ፥ እንነሳ የሚለው ተደጋጋሚ ትእዛዝ አምልኮ ለመምራት በተሰማራንበት በታ አዘውትሮ የሚያጋጥም ጉዳይ ነው። በዚህ የምናታክተው ሕዝብ ልክ የለውም። ከሚያሰለቹ ድርጊቶች የሚደመረው ሌላው ነገር መፈክር መሰል ነገሮች ምእመኑ አብሮን እንዲል የምንሰጠው ትዕዛዝ ነው። እኛ በምንፈልገው የድምጽ መጠን ማለት ካቃተውማ የት ሊገባ?

አንድን ነገር ለሰውጥ ያህል መደጋገም ነውር ባይሆንም እንግዶቻችን እስኪደናገሩ፥ ነባር ምዕመናን ምን ነካን እስኪሉ ድረስ መሪዎች እኔ የምለውን ያለ ማቋረጥ በሉ ማለታቸው አሰልቺ ነው። ይህ ደግሞ መወገድ ካለባቸው ድርጊቶች አንዱና ዋናው ነው። ሰዎችን ወደ እውነተኛ አምልኮ



የምንወስዳቸው በተለየ የመንፈስ ቅዱስ ረድኤት እንጂ እንደ ምትሃት ቃላትን ከኛ ኋላ እንዲደጋግሙ በማስገደድ አይደለም። እንዲህ አይነቱ ግዳጅ ሲበዛ ምዕመናን ይታከታሉ። እንዳናታክታቸው የሚጸየፏቸውን ነገሮች ማወቅ አለብን። ለምሳሌ በቅርቡ በአንድ የአምልኮ ሥፍራ ላይ መሪው ሰዎችን ደጋግሞ አንድን ቃል ደጋግመው እንዲሉ ሲጠይቅ ሕዝቡ ዝም በማለት ተቃውሞውን ገለጸ። በዚህ ጊዜ ብስጭት የገባው መሪ «የአባቴን ወይም የእናቴን ስም የጠራሁ መሰላችሁ ወይ?» የሚል ቁጣ የተቀላቀለበት ዘለፋ ተናገረ። ምእመኑ እንዲሰለቸን የሚያደርጉ፥ የሚያሰለቹ ወይም የሚያታክቱ ድርጊቶች መፈጸም የለብንም። ጠንካራ የተግሳጽ ቃላት እንዲሁም የእነርሱን ስሜት ያላገናዘበ ዘለፋ የሚያስለች ድርጊትን ከምንፈጽበት ሁኔታ ስለሚደመር ጠንቃቆች መሆን አለብን።

## ምክትል ለባኪነት (ገላ 5:22-23)

አንዳንዴ መሪዎች ሰባኪው የሚያጠግብ ነገር የተናገረ ካልመሰላቸው የጎደለውን ለመሙላት ይፈተናሉ። ወይም ደግሞ ሕዝቡ አይረዳውም ብለው የሚሉትን እውነት ሰባኪው እንዳካፈለ ከገመቱ ለሕዝቡ የመከለስ አዝማሚያ ያሳያሉ። በተጨማሪም ለሞኑን በውስጣቸው ሊያውጠነጥኑት ከነበረው ጉዳይ ጋር በቀጥታ ግንኙነት እንዳለው ከተገነዘቡ ነገር ሁሉ በሁለት ይጸናል ብለው ያልተነካ የመሰላቸውን ክፍል ለመጨመር ጥረት ያደርጋሉ። በሌላ ጊዜ ብዙ መናገር ልማድ የሆነባቸው መሪዎች ካሉ መቁረጫ የሌለው ንግግር ያበዛሉ። እንደ ሰባኪው ያለ ጊዜ ስለማያገኙ በዕለቱ አለኝ የሚሉትን መልካም ነገር ተንፍሰው የመውረድ ፈተና ይደቀንባቸዋል። ከላይ የጠቀስነው ጥቅስ ስለምክትል ሰባኪነት ምን ይል ይሆን? ለሚሉ እዚህ ጋ ማንሳት የፈለግነው ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ የሆነውን «ራስን መግዛት» የሚለውንና «ትእግስትን» ነው። ራሱን የሚገዛ መሪ ምክትል ሰባኪነት አይቃጣውም። ትእግስተኛም ጉድለትን በጸጋ ያሳልፋል።

ራሳቸውን የማይገዙና መታገስ የሚያቅታቸው መሪዎች ለምክትል ሰባኪነታቸው የሚሉት አያጡም። በእነርሱ አይታ በወረፋ የምትደርሳቸውን ጊዜ ጠቃሚ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል ጊዜውን እንደሰሩበት ያስባሉ።

ይፈጠራል። የሚጨበጥ መልእክት ቢተላለፍ ባልከፋ ግና ጊዜ መፍጀት ብቻ ሲሆን ለምን? ያሰኛል።

ቀደም ባሉት ዓመታት ፕሮግራም መሪው እስጸልዮ፡ አገልጋች ዘምረን፥ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ለምእመኑ የሚደርሱ መልእክቶች ከተላለፉ በኋላ በቀጥታ ወደ ዝማሬ አግልግሎት እንሄዳለን። ታዲያ በዚያ ጊዜ ከመድረኩ እንጸልይ የሚለው ይፋዊ ጥሪ በድጋሚ የሚቀርብልን ሰባኪው ሲመጣ ብቻ ነበር። አሁን አሁን ደግሞ ዘማሪያን እስጸልየውን ዝማሬያቸውን ሲቀጥሉ ይስተዋላል። በጸሎት መንፈስ ዝማሬውን እንስማ የሚል ግብግ ተደርጎልን እየሰማን ሳለ መልእክት መጥቷል እንባላለን። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ መልእክት አይመጣም የሚል የጠነከረ ተቃውሞ የለንም። ይሁን እንጂ በዚህ መስመር የተላለፉ መልእክቶችን ሲመዘኑ ቀጥተኛ፥ ግልጽና ምእመኑን የሚያንጹ እንዳልሆኑ ሲነገር ይሰማል። በተግባርም ታይቷል። ስለሆነም የቡድኑ መዘምራን ለጊዜው በተለለፉበት በዜማ መልእክተኛነታቸው ብቻ ቢስለፉ ያንጹናል። ከመካከላቸው ወቅታዊ መልእክት የሚቀበሉ የመዘምራን ቡድን አባላት ካሉ ከፕሮግራሙ አስተባባሪ ጋር ጉዳዩን አስተካክለው መልእክታቸውን ቢያስተላልፉ መልካም ይሆናል።

ስለዚህ በዚህ በኩል ያሉ ጉድለቶች ቢስተካከሉ እነርሱም ይጠቀማሉ። እኛም እንታነጻለን። ብዙ ጊዜ በቡድን ዘማሪያን መካከል በልዩ ልዩ ጉዳዮች መበታተን ሲከሰት ቁጥራቸው ያንሳል። በቁጥር ሲያንስ ለአምላኪው የፈተና እና የጥያቄ ምክንያት ከሚሆኑ አገልግሎት ባይቀበሉ ይመረጣል። ስተቀበሉም አገልግሎቱን ለመፈጸም እንዳልቻሉ ቀደም ብለው ለጋበዛቸው አካል ቢያሳውቁ ይበጃል። በተጨማሪም የተመጠነ ቁጥርና ለዕለቱ ከተመረጠው ክፍል ጋር የሚሄድ መዝሙር ለማስናዳት እንዲቻላቸው ከፕሮግራሙ አስተባባሪዎች ጋር ቅድመ ዝግጅት ቢያደርጉ የምስባኩ አገልግሎት ሀብር ያለው ይሆናል።

አይጉላ እንጂ በአንዳንድ መዘምራን ቡድን ውስጥ ከኅብረቱ ቅንጅት ያፈነገጠ አካላዊ እንቅስቃሴን በማድረግ የሕዝቡን ትኩረት የሚያዛቡ አባላት ይታያሉ። እነዚህን እንቅስቃሴዎችን የሚያሳዩትን ግለሰቦች ሕብረቱ ቢመክራቸውና ከሕብረቱ ጋር አብረው እንዲፈሱ ቢረዳቸው ሕዝቡን



ለማምለክ ያግዛሉ። አለበለዚያ የሚያመልከው ሕዝብ ለምንድነው እንዲህ የሚሆኑት? እያለ በዜማ ከማምለክ ይልቅ ወደ ታዛቢነት ዝቅ ይላል። ስለ ሶሎ ዘማሪዎች ያልናቸው አንዳንዶቹ እውነቶች የቡድን ዘማሪያንንም ስለ ሚመለከቱ በዚህ ወቅት በዚያ ሥፍራ ያነሳናቸውን የሚታረሙ ጉዳዮች ልብ ማለት ይገባል።

## 2.6 የሙዚቃ ቅንብር

ሙዚቃ ሰው እምላኩን ለማክበር የሚጠቀምበት በመሣሪያዎች እማካኝነት የሚተላለፍ መልእክት ነው። በመድረኮቻችን ብቅ ከሚሉት የፕሮግራም ዓይነቶች አንዱ በሙዚቃ የሚተላለፈው መልእክት ነው። ሙዚቃ በልብ ያደረን ደስታ ለመግለጽ የሚያገለግል ተጨባጭ መግለጫ ነው። ባለን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን እንድናመስግን በመጽሐፍ ቅዱስ ታዘናል።

«እግዘአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት
በኃይሉ ጠፈር አመስግኑት
በመለከት ድምጽ እመስግኑት
በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት።
በከበሮና በዘፈን አመስግኑት
በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት።
ድምጹ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት
እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት (መዝ 150:3-5)

ንስሃ በገባው የአባካኙ ልጅ ታሪክ እንደምናየው በዚያ ሕብረተሰብ ባህል ሙዚቃ የተለመደ የደስታ መግለጫ እንደነበረ መረዳት እንችላለን። የጌታ ምሳሌ በኅብረተሰቡ ተጨባጭ ልምድ ላይ የተመሠረተ እንደነበር እንገነዘባለን። ምክንያቱም ጌታ የሚጠቀምባቸው ምሳሌዎች በሙሉ ተጨባጭና ተግባራዊ ነበሩና። ከላይ ባነሳነው የእባካኙ ልጅ ታሪክ ውስጥ የምናየው ሁኔታ እንደሚያስገነዝበን ደስታን ለመግለጽ ሙዚቃ ሥፍራ እንደነበረው ነው። «ወደ ቤት በተቃረበ ጊዜ የሙዚቃና የጭፈራ ድምጽ

መለኮታዊና ሰብአዊ ክስተቶችን በውስጡ ያቀፈ ድርጊት ነው። በእርግጥ የእውነተኛ አገልግሎት ምንጩ ሰማይ ነው። ይሁን እንጂ በምድር ላሉ ሰዎች መልእክቱ እንዲደርስ በሰዎች ሁኔታ መቀረጽ አለበት። ስለሆነም ለዚህ ነው ደጋግመን መልእክት በሰው ቋንቋ የሚተላለፍ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው የምንለው። እግዚአብሔር ሃሳቡን ለሰዎች ለማስተላለፍ ለዋዊ መሣሪያዎች ይጠቀማል። ስለሆነም ሰባኪ ከእምላክ የተላከውን መልእክት በመድረክ ላይ ቆሞ ለተቀባዮች የሚያደርስ ማስተላለፊያ መሣሪያ ነው። በዚህ መድረክ ላይ ለመቆም ሊሟሉ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህም ለዚህ ርዕስ ተዛማጅ የሆኑትን ጥቂቶችን ጉዳዮች ብቻ በሚመለከተው መልኩ እናነሳለን።

## መልእክተኛነትና መንፈሳዊ ብቃት

ከፍጹምነት የደረሰ ሰው ባይኖርም ሰባኪያን ከእነርሱ የሚጠበቁትን መሠረታዊ የአገልጋይነት መታወቂያዎች ሊያጡ አይገባቸውም። ከማንኛውም ክርስቲያን የተለየ ጥንቃቄ በማድረግ በቅድስና ሊመላለስ እንዲሁም በአጠቃላይ ምሳሌነት ያለው ሕይወት ሊኖር ይገባዋል። ሰይጣን ወንድሞችን ይከሳል / ዘካ: 3:1-5 ራእ 12:10-11/። ምንጊዜም የጸዳ አቋም ይዘን እንድንገኝለት የሚፈልገው አምላክ «እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ብሎ ያስጣቀረጥ ይጠራናል። ይህ አምላካዊ ትዕዛዝ ዕለታዊ ትኩረታችንን የሚሻ ጉዳይ እንደሆነ ለብዙዎቻችን ግልጽ መሆን አለበት። ምክንያቱም ለመስበክ በቆምንበት መድረክ ላይ በክፋው ለተያዙት በርካታ አእምሮዎች የምንናገር ስለሆንን ከክፋው ተጽዕኖ ነጻ የሆነ በክፋው መንግሥት ላይ በሥልጣንና በድፍረት የሚዘምት ማንነት ሊኖረን ይገባል።

የመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት አስፈላጊ የሚሆንበት ሌላው ምክንያት የራሳችን አእምሮ እንዳይፈርድብን ነው። ከሕሊና ወቀሳ ነጻ ያልሆነ ሰው በሚሰብክበት ጊዜ በውስጧ ከራሱ አእምሮ ጋር ስለሚሟገት ለሌሎች ሊናገር በሚሰሙት ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ አናሳ ይሆናል። በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ንጹሕ ሕሊና ሊኖረን ግን በድፍረት እንናገራለን። መልእክታችንም ለውጥን የማምጣት ብቃቱ ይጨምራል። የሕሊና መቆሸሸ



ሊያጋጥም ከሰውም ሆነ ከጌታ ጋር በቂ ጊዜ ወስዶ ራስን በንስሃና በይቅርታ ማደስ አማራጭ የሌለው እርምጃ ነው።

የሰባኪው ሕይወት የማይከሰስ መሆን አለበት። አገልግሎትን ከሳኪው ይቀበሉታል እንጂ አይከርጁትም። «የመድረክ ላይ ስብከትህን በጥቂት ደቂቃዎች ልትጨርሰው ትችላለህ ኑሮህ ግን ሳምንቱን ሙሉ ይሰብካል።» በእርግጥ ስብከት በጥቂት ደቂቃዎች የመድረክ ትዕይንት የሚያበቃ ከመሰለን ትልቁን ስህተት እንፈጽማለን። ምክንያቱም ትልቁ ስብከታችን መጽሐፍም እንደሚል በጨለማው ዓለም ላይ የሚኖረን የብርሃንነት ሕይወት ነውና /ማቴ 5:16 1ጴጥ2:9./። እውነተኛ መልዕክተኛ የሚናገረውን የሚኖር ነው። በተጨማሪም የኖረውን የሚሰብክ ወይም ደግሞም የሚሰብከውን የሚኖር መሆን አለበት።

## መልእክተኛነትና ጥሪ

ከምንም በላይ መልእክት አቅራቢነት ጥሪን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ለሎች ነገር ማቀነባበር ስለቻሉ በመናገሪያ ምስባኩ ላይ ጌታን ወክለው መቆም የሚችሉ ይመስላቸዋል። ይሁን እንጂ ይህ ክብቃትና ችሎታ ይልቅ የእንድዩን ጥሪና ትሮታ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳነበብነው፥ ሁሉ ሐዋርያት እንዳልሆኑ ሁሉ / 1ቆሮ 12:29/ ሁሉም ወንጌልን ሰባኪዎች አይደሉም። ስለሆነም ወንጌልን ለመበበክ የሚጠሩ ሰዎች ብቻ በዚያው መስክ መሰለፍ አለባቸው /ማቴ 4:18-19/።

ጌታ ኢየሱስ አገልግሎቱን እያዩ ለነገ ይሰናዱ ለነበሩት ደቀ መዛሙርት «ወጣ ብላችሁ ወንጌልን እንዲሰብኩ ሰዎችን አሰባስቡ» ብሎ አላዘዛቸውም። ይልቁንም በማቴ 9:38 «*የመከሩ ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት*» በማለት ለሰባኪነት ሰዎች መጠራት እንዳለባቸው በቀጥታ አመለከተ። ሳይላኩ የሚሰብኩ፥ መልዕክተኞች ወይም ሰባኪዎች ሳይሆኑ ራሳቸውን ያሰማሩ ወደ ዘማቾች ናቸው። ወደ ዘማችነት ሊመች ሊቀጥሉበት ሳይመች ደግሞ ምን ቸገረኝ? በማለት መንጋውን ለአውሬ የሚያሰጥ ምያተኛነት ነው/ዮሐ 10:12-13/። ይህንን የምያተኛነት እንቅስቃሴ ጌታ በመንግስቱ ጉዳይ ላይ ሊያሰማራቸው በሚፈልጋቸው ሰዎች

ሕይወት ውስጥ ሊያየው አይሻም፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ በሮሜ 10:15-16 ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ? የሚል ወሳኝ ጥያቄ የሚጠይቀው፡፡

ከዚህ ምንባብ እንደምንገነዘበው የምሥራች አብሳሪዎች መልዕክት አስይዞ የሚልካቸው ጌታ እሳቸው፡፡ ይህንን አድርሱልኝ ተብለው አደራ የተሰጣቸው መልእክተኞች መሆን አለባቸው፡፡ ስለሆነም ምንባቡ የሚያስረዳን ሰበኪዎች የመልእክት አድራሾች እንጂ አመንጭዎች አለመሆናቸውን ነው፡፡ ይህን አድርሱልኝ የሚላቸው ጌታ ትዕዛዝ ያስፈልጋቸዋልና፡፡ አለበለዚያ በፈጠራ የተሰማሩ ወሬኞች ይባላሉ እንጂ መልእክተኞች አይባሉም፡፡ ምክንያቱም ወሬኞች ሰይጣን ክራሱ ፈጥሮ የሚያወራውን የክፋውን ተልእኮ ለማሳካት የተሰለፉ ሰፍላፊዎች ናቸው፡፡ ይህ እንዳይሆን ነበር ጌታ ደቀመዛሙርቱን መልእክት አስይዞ የላካቸው፡፡ ምክንያቱም ክርስቶስን ለማወጅ የተሰማራ ማንም በግሉ ከክርስቶስ ጋር የጠበቀና የጠለቀ ግንኙነት ሲኖረው ይገባልና፡፡ በግሉ ያጣጣመውን የጌታውን ፍቅር ለሌሎች ያውጃልና፡፡

በምስባኩ ላይ ቆመን የምናውጀው ቃል ፍላጎቶቻችንን ለመፈጸም የምንተጋበትና የራሳችንን ገድል በሰፊው የምናስተዋውቅበት መድረክ ሳይሆን ይልቁንም እግዚአብሔርን ለማገልገል ራሳችንን ለጌታ ፈቃድና ፍላጎት መጠቀሚያነት የምናቀርብበት የጌታ መሳሪያ ነው፡፡ ምስባኩ ሰባኪው ጌታ ምን እንደሚፈልግበት ተገንዝቦ ለጌታ ፈቃድ መተላለፊያ እንዲሆን ራሱን በትሕትና ለማቅረብ የሚቆምበት የተቀደሰ ቦታ ነው፡፡ ስብከትም ይህንን ለመፈጸም የሚያበችል የአምላክ መሣሪያ ነው፡፡

ቢላ ለመቁረጥ፣ ልብስ እርቃንን ለመከደን ፥ መነጽርም የዐይን ድካም ለማገዝ እንደሚጠቀሙ ሁሉ በብከትም በጌታ የተፈለገውን ሥራ ለማከናውን የተመረጠ የጌታ መሣሪያ ነው፡፡ ስለሆነም ፈጣሪ ፍጡር የሆነውን ሰው በማዘጋጀት መልእክትን በውበጡ አቆይቶ ለሚዎች በተሰናዱ ሰዓት ከእርሱ ጋር በመሆን መልእክቱን እንዲያስተሳለፍ ይገለግለበታል፡፡ ሰባኪው ፈጣሪ በፍጡር ቋንቋ መልእክቱን የሚያስተላልፍበት መሣሪያው ነው፡፡ ስለዚህ ሰባኪው እንደ እግዚአብሔር መሣሪያ የተለያዩ ሚናዎች ይኖሩታል፡፡ የሚከተሉትን ብቻ ለምሳሌ ያህል እንጠቅሳለን፡፡



## ሀ. ሰባኪው እንደ ነቢይ

በመጽሐፍ ቅዱስ ያየናቸው እያሌ ነቢያት መልእክትን ከጌታ ተቀብለው በሳኪው ኃይል መልእክቱን ለተቀባዮቹ በታላቅ ድፍረትና ኃይል ያስተላልፋሉ፡፡ ልክ እንዲሁ ሰባኪው የተቀበለውን መልእከት በእርግጠኝነትና በድፍረት ተሞልቶ በመድረክ ላይ ለለሚዎቹ ሲያውጅ እንደ ነቢያት ራሱን ለአምላክና ለሰዎች ሰጥቷል ማለት ነው፡፡ ነቢያት የሎሌነትን መንፈስ በተግባር እያሳዩ የሳኪውን ድምጽ በከፍተኛ ደረጃ ያስተጋባሉ፡፡ እነርሱ በቃሉ የሚሰለጥኑ የተውኔት ሰዎች ሳይሆኑ ለቃሉ ሥልጣን ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን ያስገዙ የቃሉ ሎሌዎች ናቸው፡፡ ደስታቸውም ሰዎች ለዚህ መልእክት ልባዊ መታዘዝን ሲያሳዩና በመልእከቱ የሳኪውን ክብር አይተው ለግደት ሲያደርጉ ማየት ነው፡፡

እዋጅ ነጋሪው ከእርሱ ደካማነት ውስንነት በሳይ የሳኪውን /የመልእክቱን ምንጭ / በጉልህ ሁኔታ በማሳየት ሳይ ብቻ ያተኩራል፡፡ ጉዳዩ ወደ መልእክቱ ባለቤት ብቻ እንዲሆን ሰዎችን ያነሳሳል፡፡ እዋጅ ነጋሪ የአዋጁ ምንጭ ባለ ሥልጣን ካልታየ እርካታ ስለሌለው እርሱ እንዲታይ የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ይከፍላል፡፡ ይህን የከበረ ዕድል ለአድማጮቹ በመስጠትም ይረካል፡፡ ሰባኪው የእግዚአብሔር መሣሪያ እንደመሆኑ የመልእክቱ ባለቤት ሎሌ መሆኑን ደጋግሞ ያስገነዝባል፡፡ ይህንንም «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» በሚለው ተደጋጋሚ ቃሉ ያስረግጣል፡፡ ሰባኪው እንደ እግዚአብሔር መሣሪያ የነቢይነት ተልእኮውን የሚወጣው እንደ እዋጅ ነጋሪ ሆኖ ነው፡፡ እዋጁንም እንዲህና እንዲህ ተብለሃል እያለ በመደጋገም ያስተጋባል፡፡

## ለ. ሰባኪው እንደ እረኛ

መጋቢው መዳቢ ባልሆነበት ሥፍራ ወቅቱን የጠበቀ የምዕመኑን ፍላጎትና ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ ሰባኪው እንደ እረኛ መንጋውን ባለበት ሁኔታ ለመድረስ የሚያስችል ምግብ ከመድረክ ያቀርባል፡፡ ለእረኛው ሰባኪ በጎች ሁሉ አንድ ዓይነትና በአንድ ደረጃ ሳይ ያሉ አይደሉም፡፡ ስለሆነም ልዩ ልዩ ሁኔታቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሚፈልጉትን ወቅታዊ እንክብካቤ